Coptic Orthodox Patriarchate
His Holiness Pope Tawadros II
Pope of Alexandria and
Patriarch of the See of St. Mark
The Papal Center

بطريركية الأقباط الأرثوذكس
قداسة البابا الأنبا تواضروس الثاني
بابا الأسكندرية
وبطريرك الكرازة المرقسية
المقر البابوي

222 Ramses St., Abbaseya, Cairo, Egypt
٢٢٢ شارع رمسيس ، العباسية ، القاهرة ، مصر
Tel: 024822580 Fax: 0235365880 email: office@popetawadros.org
تليفون: ٠٢٤٨٢٢٥٨٠ فاكس: ٠٢٣٥٣٦٥٨٨٠


*Resurrection – Amharic - 2023*

## በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ። አሜን፡፡

## ኢክርስቶስ አነስቲ ... አሊስቶስ አነስቲ፡፡

## ክርስቶስ ተነሥቶአል ... በእውነት ተነሥቷል።

ሁላችሁንም እንኳን ለ 2023 የትንሣኤ በዓል አደረሳችሁ እላለሁ። የከበረ ትንሣኤን ከዚህ ረጅም ጾም በኋላ እናከብራለን፡፡ ለ55 ቀናት የፈጀ ጾም፡፡ ትንሣኤን በየዓመቱ እንደምናደርገው እናከብራለን፡፡ እንደምታውቁት የትንሣኤ በዓል የእምነታችን መሠረት የሆነ በዓል ነው። ይህ የትንሣኤ በዓል ክርስትናን የማክበር በዓል ነው። ደግሞም በክርስቶስ የማመናችን በዓል፡፡ ስለዚህ በየእለቱ ትንሳኤውን በአግፔያ የሰዓታት ጸሎት እናከብራለን፡፡ ከዚህም በላይ በየሳምንቱ እሑድ እናከብራለን፡፡ ምክንያቱም ቀኑ የትንሣኤ እና የብርሃን ቀን ነውና። ደግሞም በየኮፕቲክ ወር በ29ኛው ቀን እናከብረዋለን፡፡ ያ ቀን የብሥራት፣ የክርስቶስ ልደት እና የትንሣኤ መታሰቢያ ነው። በየዓመቱ በከበረው የትንሳኤ በዓል እናከብረዋለን፡፡ የእኛ በዓል አከባበር እስከ 50 ቀናት ድረስ ይዘልቃል፤ እነሱም ሃምሳዎቹ ቅዱሳን ቀናት ብለን እንጠራቸዋለን፡፡ በእርግጥም የትንሣኤ ስጦታዎች በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ብዙ ናቸው። ለእናንተ ልነግራችሁ የምፈልገው በከበረ የጌታ ትንሣኤ ውስጥ ስላሉት ከከበሩ ስጦታዎች ስለ አንዱ ነው፡፡ ይህ ስጦታ ለሕይወት አወንታዊ እይታ የማግኘት ስጦታ ነው።

እግዚአብሔር የሰውን ዓይን የእይታ አካል አድርጎ ፈጠረው፡፡ በፊቱ ላይ ሁለት ዓይኖችን ፈጠረ፡፡ የአሁኑን ለማየት እና የወደፊቱን ለመመልከት፡፡ ወደኋላ እንዲያይ ብሎ በጀርባው ዓይን አልፈጠረም። ሰውን ሁልጊዜ ወደፊት የሚያይ አድርጎ ፈጥሮታል። ምንም እንኳን ሁላችንም አንድ አይነት የዓይን ቅርጽ ቢኖረንም ያ ፊዚዮሎጂያዊ እና አናቶሚካል መዋቅር ነው፡፡ ነገር ግን ስለአንድ ነገር ያለን እይታ ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ይለያያል፡፡ ስለዚህ አወንታዊ የሕይወት እይታ በሦስት ባህርያት ይገለጻል፡፡

የመጀመሪያው ባህሪው ተጨባጭ እይታ ነው፡፡ ይህ ዓይን ጉዳዩን በእውነታው፣ በገደቡ እና በቅርጹ ይመለከታል፡፡ በቅዠት ውስጥ አይደለም፡፡ በእውነታው ውስጥ ይመለከታል እንጂ፡፡ በሰውየው ፊት ነገር ሁሉ ግልጽ ነው እንጅ ሌላ ትርጉም የለውም፡ ፡

የአወንታዊ የሕይወት እይታ ሌላኛው መገለጫ ደግሞ የርኅራኄ እይታ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት የሰው ልጅ ለነገሮች ያለው አመለካከት የምሕረት ተግባርን ማካተት አለበት ማለት ነው። ምክንያቱም የምሕረት ተቃራኒው ጭካኔ ነው። ጭካኔ በአለም ላይ ብዙ ልቦችን ሞልቷል። ስለዚህም ያ አመለካከት የሰው እይታ አይደለም።

ሌላው የአዎንታዊ ራዕዩ ገጽታ፣ አካታች እይታ ነው፡፡ ያልተሟላ እይታ አይደለም፡፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት ጥቂት ውሃ ስለያዘ ጽዋ ስንናገር ይህ ጽዋ ግማሽ-ሙሉ ነው ወይስ ግማሽ-ባዶ ነው? ብለን እንጠይቃለን፡፡ አንዳንዶች በግማሽ የተሞላ ብርጭቆ ውሃ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ይህ አወንታዊ እና ሁሉን አካታች እይታ ነው። አንዳንዶች ብርጭቆውን እንደ ግማሽ ባዶ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ስለዚህ ይህ አሉታዊ አመለካከት ነው፡፡

እነዚህ ባህሪያት፡ እውነተኛ፣ ሩኅሩኅ እና አካታች እይታዎች ናቸው፡፡ ሁሉም በሕይወት ላይ ያለንን አዎንታዊ እይታ ይመሰርታሉ፡፡ ከስቅለቱና ከትንሣኤው አንዳንድ ምሳሌዎችን እሰጣለሁ፡፡

ሁለት ደቀ መዛሙርትን እናንሳ፤ ጌታ የሚወደው ዮሐንስና የአስቆሮቱ ይሁዳ። በክርስቶስ ከተመረጡት ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እነዚህ ሁለቱ የክርስቶስን ትምህርት እና ተአምራት አይተዋል፤ ደግሞም ከእሱ ጋር ነበሩ፡፡ በእርግጠኝነት፣ በእነሱና በኢየሱስ መካከል ብዙ ንግግሮች ነበሩ። የተወደደው ዮሐንስ ለሕይወት አዎንታዊ እይታ ነበረው። ወደ ጌታችን ወደ ክርስቶስ ሲቀርብ እናየዋለን። እስከ መስቀሉ እና ፈተናዎች ድረስ እንኳን እርሱን ይከተላል፡፡ ታላቅ ደስታ ሲኖረው እናየዋለን፡፡ ራሱን በጌታችን በክርስቶስ ደረት ላይ ስለማስቀመጥ ሲደሰት እናያለን፡፡ ራሱን “ክርስቶስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር” ብሎ ጠርቶታል (ዮሐንስ 19፡26)። በአንጻሩ የአስቆሮቱ ይሁዳ ፍቅረ ንዋይ የተጫነው አመለካከት ነበረው። እሱ አሉታዊ አመለካከት ነበረው፡፡ እርሱ ክርስቶስን እንደ አዳኝ እና ቤዛ አላየውም። ለዓለም መዳን የመጣ እንደሆነ አላመነም፡፡ ቁሳዊ ወይም የምድር ምኞቱን መሟላት በእርሱ ስላላገኘ፡፡ ጌታውን በሠላሳ ብር ሸጠ፡፡ በመጨረሻም ሄዶ ራሱን ሰቀለ፣ ሞተ እና ዘላለማዊ ርስቱን አጣ፡፡ ሁለቱ በአንድ ቦታ ላይ ነበሩ። አንዱ አዎንታዊ እይታ ነበረው ሌላኛው ደግሞ አሉታዊ፡፡

ሌላው በስቅለቱ ክስተት የምናየው ምሳሌ ሁለቱ ወንበዴዎች ናቸው። እነሱም በክርስቶስ ግራ የነበረው ወንበዴ እና ሌላው በክርስቶስ ቀኝ የነበረው ናቸው፡፡

አይሁድ ክርስቶስን ወንጀለኛ ነው ብለው በማመን ከጌታችን ክርስቶስ ጋር ሁለት ወንበዴዎችን ሰቀሉ። በግራ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ከጌታ ጋር ረጅም ንግግር አደረገ፡፡ "አንተ ክርስቶስ ከሆንህ ራስህንም እኛንም አድን" (ሉቃስ 23:39)፡፡ "ይህን ያለብንን ስቃይ፣ የመስቀልን ስቃይ ከኛ አርቅልን..."፡፡ በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ እይታ ነበረው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በተመሳሳይ ጊዜ እና በተመሳሳይ ምልከታዎች ውስጥ ቢሆኑም በቀኝ የተሰቀለው ሌባ አወንታዊ እይታ ነበረው። እርሱ እንዲህ ይላል፡- “እኛስ በእውነት ለሥራችን የሚገባውን ብድራት ተቀብለናልና” (ሉቃስ 23፡41)። ክርስቶስን ተመልክቶ እንዲህ አለ። "ጌታ ሆይ በመንግስትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ" (ሉቃስ 23:42) ይህ ሐረግ ታላቅ የጸሎት መግለጫ፣ የንስሐ መግለጫ ነበር፤ ልመና መግለጫ፣ የተስፋ መግለጫ፡፡ ጌታችን ክርስቶስም በቀኝ የተሰቀለውን ወንበዴ በሕይወቱ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ተቀበለው። “እውነት እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” (ሉቃ 23፥43) አለው። ይህ ምስል በሕይወት ላይ ስላለ አዎንታዊ እይታ በጣም ብዙ ምሳሌዎችን ይመለከታል፡፡ ስለዚህ ወዳጆች ሆይ አዎንታዊ እይታ ይኑራችሁ፡፡ አዎንታዊ ዓይን ነገሮችን በአዎንታዊ መልኩ ይመለከታል፡፡

ስለዚህ ወዳጆች ሆይ አዎንታዊ እይታ ይኑራችሁ፡፡ አዎንታዊ ዓይን ነገሮችን በአዎንታዊ መልኩ ይመለከታል፡፡ በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ፣ ሥራችሁ፣ አገልግሎታችሁ እና ቤተሰባችሁ በእነዚህ ሁሉ ክስተቶች ላይ አዎንታዊ እይታ ሊኖራችሁ ይገባል፡ ፡ ይህ የከበረ ትንሳኤ በሰው ሕይወት ውስጥ ያለው ተጽእኖ ነው። ሁልጊዜ ልባችሁን ከፍ አድርጉ፡፡ “ጌታ ሆይ መልካም ዓይንን ስጠኝ” በሉ። “በነገሮች ውስጥ እውነትን፣ ውበትን እና አወንታን የሚያይ"፤ "ከአሉታዊ ወይም ጠባብ እይታ ጠብቀኝ" ያ ዓይን መጥፎውን ብቻ የሚያይ ነው። ሕይወት በእያንዳንዱ መልካም ተግባር ውስጥ ሰፊ ውበት አላት።

ይህንን መልእክት ስልክላችሁ ደስተኛ ነኝ፡፡ በኮፕቲክ ቤተክርስቲያን እና በቅዱስ ሲኖዶስ ስም ልባዊ የእንኳን አደረሳችሁ መልእክቴን አስተላልፋለሁ። ከዚህ ከግብፅ፣ ለሁሉም አህጉረ ስብከት አቀርባለሁ። በመላው ዓለም ላሉ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት ሁሉ፤ ውድ ወንድሞቼን፣ አባቶች ሜትሮፖሊታን እና ጳጳሳትን እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ። አባቶች ካህናት፣ አባቶች መነኮሳት፣ እናቶች መነኮሳይያት እና የቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ አስተዳደሮች፣ ወጣቶች፣ ሁሉም አገልጋዮች፣ ሁሉም ዲያቆናት እና ሁሉም ምእመናን እና ሁሉም ልጆች በየትም ብትኖሩ ሁላችሁንም በያላችሁበት እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡ በአውሮፓ ፣ በአፍሪካ ፣ በእስያ ፣ በሰሜን አሜሪካ ፣ ደቡብ አሜሪካ ወይም አውስትራሊያ፤ ሁላችሁንም እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ። ይህን ሰላምታ ለሁሉም ርብላችኋለሁ፡፡ ከሙታን የተነሣውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እየጠየቅሁ ሁል ጊዜ ደስተኛ እንዲያደርጋችሁ እና አዎንታዊ ዓይን እንዲሰጣችሁ፡፡ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ ድርጊት እና ክስተት ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ምስጋና ለአምላካችን ይሁን። ኣሜን። ኢክሪስቶስ አነስቲ ... አሊቶስ አነስቲ

